

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

## የቀረበ የ2011 በጀት ዓመት የበጀት መግለጫ

**አብራሃም ተከስተ (ዶ/ር)**

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**ግንቦት 30/2010 ዓ.ም.**

# Budget Speech

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

በየዓመቱ እንደሚደረገው ይህ የበጀት መግለጫ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት የቀረበ ነው፡፡ ይህንን የ2011 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀት ዛሬ ለተከበረው ምክር ቤት ሳቀርብ ከፍተኛ ክብር ይሰማኛል፡፡ ያለፉት ዓመታት በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች በርካታ ስኬቶች የተመዘገቡባቸው ዓመታት ቢሆኑንም በዚያው ልክ ደግሞ በርካታ ተግዳሮቶች የተስተናገዱባቸው ነበሩ፡፡ በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን ልዩ ልዩ ክፍሎች የተፈጠረው አለመረጋጋት ለመንግስታችን ፈታኝ ሁኔታን ፈጥሮ የነበረ ሲሆን፣ ችግሩን በዲሞክራሲያዊ አግባብነት ለመፍታት በተደረገው ሙከራ በአንጻራዊ መልኩ አሁን በሀገሪቱ ሰላም ተፈጥሯል፡፡ እንደዚሁም የፊሲካል ፖሊሲያችን የሀገራችንን ልማት ግቦች ለማሳካት የሚያስችል ሆኖ የተቀረጸም ቢሆንም ውጤታማ እንዳይሆን በተግባራዊነቱ በኩል በከፍተኛ ፈተናዎች የታጠረ ነበር፡፡ በመሆኑም የዚህ ዓመት የበጀት ንግግሬ በአመዛኙ በበጀት ዲሲፕሊን ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

የመግለጫው ይዘት በቅድሚያ ባለፉት ዓመታት የአገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ ያሳየውን አፈጻጸምና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን፣ የመንግሥትን የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸምና የወደፊት የትኩረት አቅጣጫ ለመጠቆም እሞክራለሁ፡፡ እንዲሁም በመገባደድ ላይ ያለውን የበጀት ዓመት ዕይታ በአጭሩ ካመለከትኩ በኋላ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተደግፎ የቀረበውን የ2011 የፌዴራል መንግስት በጀት ድልድል ከተመሠረተባቸው ታሳቢዎች ጋር የተከበረው ም/ቤት ተመልክቶ እንዲያጸድቀው አቀርባለሁ፡፡

## የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2008 በጀት ዓመት ተከስቶ ከነበረው የኤልኒኖ ዝናብ እጥረት ጋር በተያያዘ ካጋጠመው መቀዛቀዝ ተላቆ በ2009 በጀት ዓመት የ10.9 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ የዕድገቱን ቀጣይነት አረጋግጧል፡፡ ይህም ለተከታታይ 14 ዓመታት የተመዘገበ ፈጣን ዕድገት ሲሆን፣ በነዚህ

ዓመታት ኢኮኖሚው በአማካይ በየዓመቱ በ10.6 በመቶ አድጓል፡፡ ይህ በተከታታይ ዓመታት የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገትም ዓመታዊ የዜጎች አማካይ የነፍስ-ወከፍ ገቢ ወደ 863 የአሜሪካን ዶላር ከፍ እንዲል ያስቻለ ሲሆን፣ ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ህብረተሰብ ብዛትም እንዲቀንስ በማድረግ የሀገሪቱ የድህነት ምጣኔ በ2008 ዓ.ም ወደ 23.5 በመቶ ዝቅ እንዲል አስችሏል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት በአንጻራዊነት ሲታይ አሳታፊና ፍትሃዊ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ሆኖም ህብረተሰቡን በላቀ ሁኔታ ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱንና አሁንም በሀያ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በድህነት ውስጥ እንደሚገኙ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡ በከተሞች ያለው የሥራ አጥነትም የመቀነስ አዝማሚያ ያሳየ ቢሆንም አሁንም የሥራ አጥነት ምጣኔው 16.9 በመቶ (በ2008) በመሆኑ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡

በ2009 የተመዘገበው ዕድገት ከአቅርቦት አንጻር በሁሉም ዋና ዋና ዘርፎች ከተመዘገበው የምርትና አገልግሎት ዕድገት የመነጨ ቢሆንም፣ 68 በመቶ ያህሉ የተገኘው ግን ከአገልግሎትና ከኮንስትራክሽን ዘርፎች እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የግብርናው ዘርፍ የ6.7 በመቶ ዕድገት በማስመዝገቡ በ2009 ለተገኘው የ10.9 በመቶ ዕድገት 23 በመቶ ገደማ አስተዋጽኦ ሲያበረክት፣ አምራች ኢንዱስትሪው ደግሞ 9.6 በመቶ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከፍላጎት አንጻር ለተመዘገበው ዕድገት ደግሞ የግልና የመንግስት ኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ እንዲሁም የግልና የመንግስት ፍጆታ በጎ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሲሆን፣ ኤክስፖርት በአንጻሩ ለዕድገቱ አሉታዊ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡

ፈጣንና ፍትሀዊ ዕድገቱን ለማስቀጠልና የኢኮኖሚውን ተጋላጭነት ለመቀነስ የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ለውጥ የማረጋገጥ ግብ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር በ2009 የአምራች ኢንዱስትሪው ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ የነበረው ድርሻ 6.4 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ይህም ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት አማካይ አንጻር እንኳን ሲታይ ግማሽ ያህል ብቻ በመሆኑ አሁን የተደረሰበት የኢኮኖሚ ዘርፍ ሽግሽጉ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም አምራች ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋት ለዘርፉ ኢንቨስትመንት መጎልበት አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማነቆ የሆኑ ተግዳሮቶችን በአግባቡ መፍታት አንገብጋቢ ተግባር መሆኑን ማስታወስ እወዳለሁ፡፡ የአምራች ኢንዱስትሪው በአለመጠናከሩ የኤክስፖርት ዘርፉም መዋቅራዊ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንጻር የበኩሉን ድርሻ የሚጠበቀውን ያህል መወጣት ባለመቻሉ ሥራ አጥነት አንዱ የአገሪቱ ማህበራዊ ችግር ሊሆን ችሏል፡፡

የኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ለውጥ በራሱ ጊዜ የሚከሰት ሳይሆን ልማታዊ መንግስታት አቅደው የሚሰሩበት ሂደት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ እንዲሁም ለግሉ ዘርፍ አመች ሁኔታዎችን በመፍጠር ከፍተኛ ሚና መጫወቱ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ዕውን ለማድረግ መንግስት የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የመሠረተ ልማትና የኢነርጂ ልማት ፕሮግራሞችን፣ እና ሌሎች የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎችን አጠናክሮ ሲተገብር የቆየ ሲሆን፣ ትራንስፎርሜሽኑን የሚያፋጥኑ አምራች ዘርፎችም በቀጥታ እየተሳተፉ መጥተዋል፡፡ ከዚህም በላይ በክልሎች የተጀመሩ የአግሮ ኢንዱስትሪ ክላስተሮች ግንባታ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቱ ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ለማድረግ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በቀጣይ ትርጉም ያለው አፈጻጸም እንዲያሳዩ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግሥት የጀመራቸውን የተለያዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የጎለበተ ካልሆነ የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ለማምጣትም ሆነ ዕድገቱን ቀጣይ ለማድረግ አዳጋች መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመሆኑም የግሉ ዘርፍ በተገነቡት የኢንዱስትሪ ፓርኮች በመግባት፤ በነጻ ተወዳዳሪነት በማምረት ተግባር ላይ በመሳተፍ ለአገር ዕድገት የሚያደርገውን አስተዋፅኦ ማጎልበት ይኖርበታል፡፡ የግሉን ዘርፍ አስተዋጽኦ ይበልጥ ለማሳደግ የመንግሥትና የግል ዘርፍ ሽርክና አሰራርን ለመተግበር የሚያስችል የህግና የአደረጃጀት ስርዓቶች የተዘረጉ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በሽርክና ሊሰራባቸው የሚችሉ የኢንቨስትመንት ዓይነቶችን በመለየት ባለሀብቱ እንዲሳተፍ የማበረታታት፤ አቅጣጫ የማስያዝና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዕቅድ ተይዞ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተለይ ባለፉት ዓመታት መንግሥት በወሰዳቸው የተቀናጀ የፖሊሲ፤ አስተዳደራዊና ተቋማዊ ተግባራት አገራችን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ያስመዘገበችውን ውጤት አስጠብቆ መቀጠል ተገቢ ይሆናል፡፡ ለዚህም በቅርቡ በሀገሪቱ ያጋጠመው አለመረጋጋት ቀደም ሲል የገነባነውን በጎ ገጽታ እንዳይሸረሽርና በሀገር ውስጥና በውጭ የግል ኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር የተጀመረውን የማረጋጋት ጥረት በመቀጠል የተገኘውን የኢንቨስትመንት ፍሰት ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይገባል፡፡

ባለፉት ዓመታት በታየው የፋይናንስ ተቋማት መስፋፋት፤ ለቁጠባ የሚከፈለው የወለድ መጣኔ ከፍ እንዲል መደረጉ፤ ህብረተሰቡ ስለ ቁጠባ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ በተደረገው ጥረት፣ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ አማካይነት የሀገሪቱ የቁጠባ እና ኢንቨስትመንት ሁኔታ ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት የአገር ውስጥ የቁጠባ ምጣኔ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ድርሻ በ2003 ከነበረበት 17.2 በመቶ በ2008 ወደ 22.4 በመቶ ከፍ ማድረግ

የተቻለ ሲሆን በ2009 ደግሞ ወደ 24.1 በመቶ አድጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ምጣኔ በ2003 በጀት ዓመት 32.1 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ2009 በጀት ዓመት ደግሞ ይህ ምጣኔ ወደ 39 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በሌላ በኩል ከ2003 እስከ 2005 በነበሩት ዓመታት በኤክስፖርት አፈጻጸም መሻሻል የታየ ቢሆንም የወጪ ምርቶቹ በተወሰኑ የግብርና ምርቶች ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ከዓለም የሸቀጦች ዋጋ መውደቅ፣ ከምርታማነትና ከማምረት አቅም ማነስ፣ በሀገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት ፈጥሮ እና የኤክስፖርት ምርቶችን በዓይነትና በመጠን ለማሳደግ ባለው የአቅም ውስንነት የተነሳ ከ2006 ዓመት ጀምሮ ዕድገቱን ማስቀጠል አልተቻለም፡፡ ከኤክስፖርት የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ አፈጻጸም ደካማ በመሆኑም ለልማት የሚያስፈልጉንን የካፒታልና ጥሬ ዕቃዎች፤ እንዲሁም በአገር ውስጥ የማይመረቱ መሰረታዊ ሸቀጦችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ፈታኝ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የኤክስፖርት አፈጻጸማችን ደካማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሀገራችንን ልማት ለማፋጠን የሚረዳውን የውጭ ፋይናንስ በተለይም የንግድ ብድር ለማግኘትና ለመጠቀም ዋናው ዕንቅፋት ሊሆን ችሏል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም በኢንቨስትመንት እና በቁጠባ መካከል ያለውን ልዩነት ለመሸፈን የውጭ ብድር ከፍተኛ ሚና የነበረው ቢሆንም ከኤክስፖርት አፈጻጸም መቀዛቀዝ ጋር ተዳምሮ የኢንቨስትመንት ዕድገቱን ቀጣይነት አሳሳቢ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም የኤክስፖርትን ገቢ ለማሳደግ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማጎልበት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ እና የሀገር ውስጥን ገቢ ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኤክስፖርትን ለማሳደግ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲያችንን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ በቅርቡ የተደረገው የብር የውጭ ምንዛሬ ማሻሻያ (Currency Devaluation) እርምጃ ተወስዷል፡፡ ይህም እርምጃ ከሌሎች ማስተካከያዎች ጋር ተዳምሮ ውጤት ያመጣል የሚል እምነት ተጥሎበታል፡፡

የዋጋ ዕድገት ባለፉት ዓመታት የኢኮኖሚው ፈታኝ ችግር እንደነበረም ይታወሳል፡፡ ሆኖም በመንግሥት በኩል ተግባራዊ በተደረጉ ጥብቅ የፊስካልና የሞኒታሪ ፖሊሲዎች እንዲሁም የመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን አቅርቦት ለማሳደግ በተደረገው ጥረት እና በተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የዋጋ ንረቱን ለማርገብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በ2009 በጀት ዓመት አጠቃላይ የ12 ወራት ተንከባላይ አማካይ የዋጋ ንረት 7.2 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ ይህም በዕቅዱ በተያዘው ግብ

መሠረት የተከናወነ ነው፡፡ ነገር ግን በያዝነው በጀት ዓመት የዋጋ ንረቱ በሁለት አሀዝ በሚገለጽበት ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ይህም በአመዛኙ ከምግብ ሸቀጣሸቀጦች መወደድ ጋር ተያይዞ የተከሰተ ነው፡፡ ለዚህም በሀገራችን ተከስቶ የነበረው አለመረጋጋት የገበያውን አቅርቦት ሥርጭት በማዛባቱ የተከሰተ ከመሆኑም ባሻገር በግብይት ሥርዓቱ ከሚታዩ ችግሮች ጋር ተያይዞ የተከሰተ አግባብነት የሌለው የዋጋ ጭማሪም አስተዋጽኦ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት የፖለቲካ መረጋጋቱን ተከትሎ ከመጋቢት ወር ጀምሮ የወርሃዊ ዋጋ ዕድገቱ እየቀነሰ መምጣቱን ማየት ተችሏል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በጥቅሉ የአገራችን ኢኮኖሚ ፈጣንና በአንጻራዊ ሁኔታ ከፍተኛ ዕድገት ማስመዝገቡን የቀጠለ ቢሆንም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉት የአምራች ኢንዱስትሪና የኤክስፖርት ዘርፍ ጉልህ መዋቅራዊ ለውጥ ያላሳዩ በመሆኑ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሆኑትን የውጭ ምንዛሬ የማፍራትና የስራ እድል የመፍጠር ዓላማን በሚጠበቀው መልኩ ማሳካት አልተቻለም፡፡ የ2011 በጀት የትራንስፎርሜሽን አጀንዳን፣ የኢንዱስትሪ ልማትንና የኤክስፖርት መስፋፋትን እንዲሁም የሥራ ዕድል መስፋፋት የማድረግ አቅጣጫን እንዲከተል ተደርጓል፡፡

# የፊሲካል ፖሊሲ አፈጻጸም

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

መንግሥት የኢኮኖሚውን አቅጣጫ ከሚመራበትና በጉልህም ከሚሳተፍባቸው ዓበይት የፖሊሲ መሳሪያዎች በዋናነት የሚጠቀሰው የፊሲካል ፖሊሲ ነው፡፡ የፊስካል ፖሊሲው ተግባራዊ የሚሆነው በየዓመቱ በሚዘጋጀውና ሥራ ላይ በሚውለው ዓመታዊ በጀት ሲሆን ይህም በዘመኑ በሚኖረው የገቢ፣ ወጪና የበጀት ጉድለት አሸፋፈን አማካይነት ነው፡፡ ዓመታዊ በጀቱ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣንና ቀጣይ ሆኖ የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ ጅምሩን ለማስቀጠል እንዲሁም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ባለፉት ዓመታት የመንግስት የወጪ በጀት በአመዛኙ በሀገር ውስጥ ገቢ የሚሸፈንበትን አቅም ለመፍጠር ጥረት የተደረገ ሲሆን የበጀት ጉድለቱም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር በሚያግዝ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

የመንግስት ወጪም በአብዛኛው የዘላቂ ኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት የሆነውን የሰው ሀብት ለማጎልበትና የመሠረተ ልማት ማስፋፋት እንዲሁም ድህነትን ለመቀነስ በሚረዱ ዘርፎች ልማት ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የፊስካል ፖሊሲው መንግሥት በሚያደርገው ኢንቨስትመንት ዘላቂ የሆነ ኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሲሆን፣ የመሠረተ-ልማቶችንም በማስፋፋት የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴ በአዎንታዊ መልኩ የሚያግዝ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ባለፉት ዓመታት የመንግስትን ወጪ ለመሸፈን ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታና ብድር ምንጮች የመንግስት ገቢ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተለይም የታክስ ገቢን ለማሳደግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመመደብ የታክስ አሰባሰቡ በዘመናዊ የመረጃና ቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲሁም በአደረጃጀትና የሰው ኃይል እንዲታገዝ በማድረግ የታክስ ገቢ ዕድገት እንዲያሳይ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ሆኖም የታክስ ገቢው ዕድገት በተፈለገው መጠን አጥጋቢ ሊሆን አልቻለም፡፡ በመሆኑም የታክስ ገቢው ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2007 ከነበረበት 12.7 በመቶ በ2009 ወደ 11.6 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ የታክስ አሰባሰቡ ዕድገትም ሆነ በየዓመቱ ከሚታቀደው አንጻር ያለው አፈጻጸም ከዓመት ወደ ዓመት እያሽቆለቆለ መምጣቱንም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከ2004-2007 ባሉት ዓመታት የታክስ ገቢ በአማካይ በየዓመቱ በ31 በመቶ ያድግ የነበረ ሲሆን፣ በ2008 እና በ2009 በቅደም ተከተል ያሳየው ዕድገት ወደ 15.2 እና 10.3 በመቶ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ እንዲሁም ከዓመታዊ ዕቅዱ የሚያሳየው አፈጻጸም እያሽቆለቆለ የመጣ ሲሆን፣ በ2009 በጀት ዓመት ከተያዘው የፌዴራል መንግስት የገቢ ዕቅድ ውስጥ 38 ቢሊዮን ብር ሳይሰበሰብ መቅረቱ ይታወሳል፡፡ በ2010 በጀት ዓመትም እስከ አሁን ከታየው አፈጻጸም አንጻር ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ከተያዘው ዕቅድ እንደማይሰበሰብ ተገምቷል፡፡ የዚህ ዕንደምታ በመንግስት ወጪ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር የልማት ፕሮጀክት ሥራዎች ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት እንዲሸጋገሩ በማድረግ የበጀት ጫና መፍጠር ከመሆኑም በላይ ለህብረተሰቡ መድረስ ያለበት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እየተጓተተ እንዲሄድ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የታክስ ገቢ አሰባሰብ ጉዳይ በመንግስትና በህብረተሰቡ ከፍተኛ ትኩረት ማግኘት ያለበት አጀንዳ እየሆነ መጥቷል፡፡

ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ ደካማ መሆን በዋናነት ለአገሪቱ ምርት ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ታክስ የማይሰበሰብባቸው ዘርፎች መኖራቸውን በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡ የአገሪቱ የታክስ አቅም ከፍተኛ መሆኑንና ዋናው የታክስ አፈጻጸም ችግር በታክስ አሰባሰቡ ረገድ መሆኑን የተካሄደው ጥናት አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የታክስ ሰብሳቢው መዋቅር ሁለንተናዊ አቅም ፈጥኖ መጠናከር ይኖርበታል፡፡ በተለይም የታክስ ኦዲት አቅምን ማሳደግ፣ የመረጃ

ሥርዓቱን ማዘመን እና መረጃውን ለታክስ ግመታ የመጠቀም አቅምን ማጎልበት፣ የታክስ አስተዳደር አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግና የህግ ተገዥነትን ማስፈን ለታክስ አሰባሰቡ መሻሻል ወሳኝ ጉዳዮች በመሆናቸው በቀጣይ እነዚህን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህም ባሻገር መሻሻል ያለባቸውን የታክስ ፖሊሲና ህጎች በመለየትና የተጀመሩ ጥናቶችን በማጠናቀቅ የህግ ማሻሻያዎች ከ2011 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን ለተከበረው ምክር ቤት ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ በታክስ አሰባሰብ ረገድ የታየውን አፈጻጸም ፈጥኖ ለማሻሻል የመንግስት ቁርጠኝነት ወሳኝ በመሆኑ በቀጣይ መንግስት ለታክስ አጀንዳ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡ በታክስ አሰባሰብ የታየውን አሳሳቢ መዳከም ለመቀልበስ ከታክስ ሰብሳቢ መዋቅሩ ውጭ ያሉ የባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት እና ተቀናጅቶ መስራትን የሚጠይቅ በመሆኑ ከወዲሁ የተለየ እንቅስቃሴ ለማድረግ የጋራ ጥረት ማድረግ የግድ ይላል፡፡ እነዚህ በፌዴራልም ሆነ በብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት በኩል እየተደረጉ ያሉና በቀጣይም ለመተግበር የታቀዱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ታክስ ከፋዩን ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ልምድ እንዲያዳብር የሚያግዙ እና በተጓዳኝም መረጃን መሰረት በማድረግ ታክስ የመክፈል ግዴታን ለመወጣት የሚያስገድዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

የመንግስትን ወጪ በሚመለከት ባለፉት ዓመታት ጠቅላላ የመንግስት ወጪ በአማካይ በ23.3 በመቶ ያደገ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ድህነትን ለመዋጋት ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ላይ የዋለው ወጪ በአማካይ በ22.5 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በ2009 በጀት ዓመት ከተደረገው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ 63.1 በመቶ የሚሆነው ዕድገትን ለማፋጠንና ድህነትን ለመቅረፍ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ቅድሚያ ለተሰጣቸው የማህበራዊና የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ፕሮግራሞች ወጪ መሸፈኛ የዋለ ነው፡፡

የመንግስት ዕዳን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አማካኝነት ለሚከናወኑ የልማት ተግባራት የኮመርሻል ውጭ ብድር በመወሰዱ ምክንያት እና የኤክስፖርት አፈጻጸም በመዳከሙ የሀገሪቱ የውጭ ብድር ጫና ስጋት ከፍ ሊል ችሏል፡፡ በመሆኑም የኤክስፖርት አፈጻጸም እስከሚሻሻል የኮመርሻል ውጭ ብድር እንዲገደብ ተደርጓል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ደግሞ የኮርፖሬት አስተዳደራቸውንና ተወዳዳሪነታቸውን በማሻሻል በወሰዷቸው ብድሮች የጀመሯቸውን ፕሮጀክቶች በውጤታማነት በማጠናቀቅ ለኤክስፖርት መሻሻልና ለያዝነው የትራንስፎርሜሽን አጀንዳ መሳካት አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ባለፉት ዓመታትም ሆነ ዘንድሮ የመንግስት የወጪ አስተዳደሩን ዘመናዊና ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተከናወኑ የማሻሻያ ስራዎችም ውጤቶች የተገኙ ቢሆንም በርካታ መስሪያ ቤቶች በጥናት ተደግፈው ሥራ ላይ የዋሉ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓቶችን ተከትለው የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በማዋል ረገድ ፍላጎቱና ዝግጁነቱ እንደሚጎድላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህ መ/ቤቶች ዕቅድና በጀትን፣ እንዲሁም የሂሳብና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶችን በወቅቱና በጥራት አዘጋጅቶ አለማቅረብ፣ የኦዲት ግኝቶችን እና የአሰራር ክፍተቶችን በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ያለማስተካከል ድክመቶች ይታይባቸዋል፡፡ እነዚህንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ባለፉት ሁለት ዓመታት የፋይናንስ ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩ በርካታ የህግና የአሰራር ማሻሻያዎች፣ ተከታታይ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች እንዲሁም በአጥፊዎች ላይ የቅጣት እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ እነዚህ የተወሰዱ እርምጃዎች ያስገኙትን ውጤት በዝርዝር ለማየት እንደሚከተለው እገልጻለሁ፣

- ከ2009 በፊት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት የማቅረብ ከፍተኛ ችግር ይታይባቸው ነበር፡፡ ለአብነትም በ2008ና ከዚያ በፊት በነበሩት ዓመታት ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርታቸውን በወቅቱ የሚያቀርቡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች 20% እንዲሁም ዓመታዊ ሂሳባቸውን የሚያቀርቡ 69% ያህሉ ብቻ ነበሩ፡፡ የወሰዱትን በጀት አጠቃቀም በተመለከተ የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ የማያቀርቡትን ኃላፊዎች ተጠያቂ ለማድረግና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት በተደረገው እንቅስቃሴ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርት የሚያቀርቡ 80% የደረሱ ሲሆን፣ ዓመታዊ ሂሳባቸውን በወቅቱ ዘግተው የሚያቀርቡ ከጠቅላላው የመንግሥት መ/ቤቶች 95% ደርሰዋል፡፡
- የባለበጀት መ/ቤቶች የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸውን ለማጠናከር የውስጥ ኦዲተሮችን የሙያ ነፃነት ለማጎልበት አስተዳደራዊ ተጠሪነታቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ አሰራርም የውስጥ ኦዲተሮች የተሻለ የውስጥ ኦዲት፣ የቁጥጥርና ክትትል ስራዎች ማድረግ ያስቻላቸው ሲሆን የፋይናንስና የግዥ ሥርዓቱ እንዲጠናከር ማገዙም ታይቷል፡፡ በዚህ ረገድም ከ2008 በፊት ወቅታዊ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ያቀርቡ የነበሩ መስሪያ ቤቶች ብዛት 18% ብቻ የነበሩ ሲሆን፣ በ2010 በጀት ዓመት ወቅታዊ ሪፖርት ያቀረቡ 90% ደርሰዋል፡፡ አሁንም ግን በውስጥ ኦዲት መዋቅሩ በራሱ የሚታዩ የአመለካከትና የሙያ ብቃት መጓደል፣

እንደዚሁም ኃላፊዎች ለውስጥ ኦዲት የሚያደርጉት ድጋፍ የተሟላ አለመሆን የተነሳ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ይህንኑ ለመቅረፍም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ተጨማሪ ልዩ ክትትሎችን የማካሄድ ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ባደረገው ኦዲት የሚያቀርባቸውን የኦዲት አስተያየቶችና ግኝቶች እንዲስተካከሉ ለማድረግ ዝርዝር መርሃ ግብር በማዘጋጀት በመስክ ጉብኝት ጭምር የተደገፈ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ በመነሳትም በ2009 እና 2010 በጀት ዓመታት የክትትል፤ የኦዲትና የድጋፍ ስራን በማጠናከር በ59 መስሪያ ቤቶች የተደረጉ የእርምት እርምጃዎች ላይ ዝርዝር የክትትል ኦዲት ሪፖርት በማዘጋጀት ለአስፈጻሚና ለሕግ አውጪው አካላት ቀርቧል፡፡ ሪፖርቱ በዋና ኦዲተርና በውስጥ ኦዲት ግኝቶች መሠረት በህግ የሚጠየቁት በህግ እንዲጠየቁ፣ መወራረድ ያለባቸው ሂሳቦች እንዲወራረዱ፣ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ መደረጋቸውን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ከክትትል ሪፖርቱ መገንዘብ እንደሚቻለው በግኝቶቹ መሠረት ማስተካከያ ያደረጉ መ/ቤቶች ያሉትን ያህል ለማስተካከል ዝግጁ ያልሆኑ መ/ቤቶችም እንዳሉ ታይቷል፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር እነዚህን መ/ቤቶች በሥርዓቱ መሠረት ተጠያቂ ማድረጉን የሚቀጥል ሲሆን፣ የተከበረው ም/ቤትም በቀረበው ሪፖርት መሠረት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲሰጥ በማክበር እጠይቃለሁ፡፡
- ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ በየሩብ ዓመቱ በአጠቃላይና በአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ደረጃ የመንግስት ፋይናንስ አተዳደር አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን የሚመለከት ዝርዝር ሪፖርት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ የፋይናንስ ተጠያቂነት ስርዓቱ እንዲጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡
- የፋይናንስ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ ኃላፊዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ የሚያስችል መመሪያ ወጥቶ ከመጋቢት 2009 ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረትም የበጀት አፈጻጸም፣ የሂሳብ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶችን በመመሪያው በተቀመጠው የማቅረቢያ ጊዜ ባለመቅረባቸው እስከአሁን ለ104 መ/ቤቶች የበላይ እና የሚመለከተታቸው የፋይናንስ ኃላፊዎች ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ገንዘብ የሚደርስ አስተዳደራዊ ቅጣት ተወስዷል፡፡
- ተጠያቂነትን በማረጋገጥ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓቱን ለማጠናከር ከተከናወኑ ከነዚህ ተግባራት በተጨማሪ የመዋቅሩን አቅም ለመገንባትም በርካታ ስራዎች ጎን ለጎን ተከናውነዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹም፣

- የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን የፋይናንስ አስተዳደር አቅም በባለሙያዎች ለማጠናከር 700 ያህል የጀማሪ ባለሙዎች አዲስ የስራ መደቦች ለተለያዩ መ/ቤቶች በማስፈቀድ በባለሙያ እንዲሟሉ የተደረገ ሲሆን፣ እነዚህ ጀማሪ ባለሙያዎችን ለስራው ዝግጁ ለማድረግም ከ3 ሳምንት እስከ 1 ወር የሚደርስ ስልጠና ተቋማዊ በሆነ አግባብ ተሰጥቷል፡፡
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስርዓቱን የቁጥጥር ተግባር ይበልጥ ለማጠናከር፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ስራዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም በፌዴራል ደረጃ ለሚገኙ የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ስርዓት /IFMIS/ ለመዘርጋት ታቅዶ ስራው በተጠናከረ ሁኔታ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ እስከ አሁንም በ36 መስሪያ ቤቶች ስርዓቱ ተዘርግቷል፡፡
- በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር የታዩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍና ይበልጥ ዘመናዊ ለማድረግ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡ በቀጣይም የፋይናንስ አስተዳደሩን ጨምሮ ዝርዝር ማስፈጸሚያ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና ሌሎች ሰነዶች የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡ የመንግስት ግዥ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለማከናወን የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ማካሄድ ተጀምሯል፡፡

- በሦስተኛ ደረጃ የመንግስት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓትን ለማጠናከር እንዲቻል ትኩረት ተሰጥቶ የተከናወነው ተግባር ውዝፍ ሂሳቦችን ለማጥራትና ያለአገልግሎት የተከማቹ ንብረቶችን ማስወገድን የሚመለከቱ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹ፣
  - ለረዥም ግዜ እየተንከባለሉ የመጡ ሂሳቦችን በተመለከተ ከመዝገብ መሰረዝ ያለባቸው ሂሳቦች ታይተው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማስቻል መ/ቤቶቹ ዝርዝር መረጃ የያዘ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በተጠየቀው መሠረት 16 መ/ቤቶች መረጃውን ያቀረቡ ሲሆን፣ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብና ለማስወሰን ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡
  - በየመስሪያ ቤቶች ለረዥም ዓመታት ተከማችተው የነበሩ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን እስከ ሰኔ 2010 ሙሉ ለሙሉ እንዲወገዱ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተነድፎ በተደረገ ክትትል መሰረት በርካታ መስሪያ ቤቶች አላስፈላጊ ንብረቶችን አስወግደው እስከ ግማሽ ዓመቱ ብቻ ከነዚህ ንብረቶች ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡ የተወሰኑ ባለበጀት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ንብረትን ለማስወገድ ዝግጁነት የጎደላቸው ሆነው በመታየቱ አስፈላጊው ክትትል እየተደረገ ነው፡፡

በመጨረሻም የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን በማጠናከር ረገድ ትኩረት ተሰጥቶ የተከናወነው የህዝብ ተሳትፎን የማጠናከር ስራ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ በፌዴራል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሁሉም መስሪያ ቤቶች ተሰራጭቷል፡፡ በተለይም በርካታ ፕሮጀክቶችን ለሚያስፈጽሙና ከፍተኛ በጀት ያላቸው መስሪያ ቤቶች ትኩረት በመስጠት ስርዓቱን ተግባራዊ እንዲያደረጉ ለማድረግ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ሥልጠና ተሰጥቶ አተገባበሩ ላይ ጥብቅ ክትትል በመደረግ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ባለፉት ሁለት ዓመታት በ350 ወረዳዎች ዜጎች የቅድመ በጀት ውይይቶች እንዲያደርጉ በማድረግ በመንግስት ፋይናስ አስተዳደርና ቁጥጥር ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ እንዲጠናከር ተደርጓል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በያዝነው በጀት ዓመትም አላስፈላጊና ውጤታማ ያልሆኑ የመንግሥት ወጪዎችን በመቀነስ የበጀት ቁጠባ በማድረግ ለልማት ወጪዎች ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህንንም ውጤታማ ለማድረግ ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች ጋር ምክክርና ውይይት የተደረገ ሲሆን አሰራሩም ስርዓት እንዲኖረው መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህ ሂደትም የመንግሥት መ/ቤቶች ከበርካታ ውጤታማ ካልሆኑ ወጪዎች በመገደብ የበጀት ቁጠባ እንዲያደርጉ የሚያግዝ ስትራቴጂ ተላልፏል፡፡ ይህ ስትራቴጂ ተግባራዊ ከሆነ በኋላም ብር 370 ሚሊዮን ለመንግስት ተመላሽ ሆኖ ለተለያዩ ወጪዎች ፋይናንስ ለማድረግ ጥቅም ላይ ለማዋል ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ስልቱን ለማስፈጸም በተደረገው ጥረት ስለ ወጪ ቁጠባ ያለው ግንዛቤም ተሻሽሏል፡፡ ሆኖም አሁንም በመንግስት መ/ቤቶች ዘንድ የህዝብ ገንዘብና ንብረትን በቁጠባ በመጠቀም ላይ ያለው አመለካከት ብዙ የሚቀረው በመሆኑ በአንድ በኩል አሰራሮችን ጠበቅ በማድረግ፣ ዝግጁነት በሌላቸው ላይ ደግሞ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

እስከ አሁን የተገኙትን ውጤቶች መነሻ በማድረግ የአገራችንን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ተግባር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሁሉንም ዜጋ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይ

በዘርፉ የሚከናወኑ ተግባራትን ማስታወስ በጋራ ለምናደርገው ጥረት ጠቃሚ መሆኑን ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥርን በቀጣይ ይበልጥ ዘመናዊ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን የሚያስችል ከ2010 አስከ 2014 የሚቆይ ሁሉን ዓቀፍ የሆነ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡ ስትራትጂው ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተገናዘበ እንዲሆን እና ዕድገቱንም በሚያግዝ መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን፣ የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ይበልጥ ዘመናዊ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል በሚከተሉት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

- የፕሮግራም በጀት ስርዓትን ውጤታማነት ማረጋገጥ፤ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት የፕሮግራሞች፣ ፕሮጅክቶችና፤ ተግባራት ውጤታማነትን ዕውን ማድረግ፣ የውጤት ስምምነት በመፈራረም ተጠያቂነትን የማስፈን እና የፕሮጀክቶችን ሙሉ ሰነዶች በማደራጀት ክትትሉን የማጠናከር ስራዎችን ማከናወን፤
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደሩን ዘመናዊ ለማድረግ የተጀመሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራዎችን ማጠናቀቅና የግዢ ስርዓቱን ለማዘመን የመንግስት ግዥ በኤሌክትሮንክስ ዘዴ የሚፈጸምበት ስርዓት ስራ ላይ ማዋል፣
- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር የህግ ማዕቀፍና አደረጃጀትን ማሻሻልና የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቱን ማጠናከር፣
- የማዕከል ግዥ ፈጻሚ አካልን አደረጃጀት ማጠናከር እና በማዕከል የሚገዙ ዕቃዎች ጥራትና ወቅታዊነትን ማረጋገጥ፣
- የጥሬ ገንዘብ አስተዳደርና ክፍያ ስርዓቱን ይበልጥ ዘመናዊ ለማድረግ የነጠላ ትሬዥሪ ስርዓትን በመላ አገሪቱ የመዘርጋትና የማጠናከር ስራዎች መተግበር፤
- የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ዓለም ዓቀፍ የመንግስት የሂሳብ አያያዝ ደረጃን ሙሉ በሙሉ እንዲከተል ጥናቶችና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፤
- የመንግስት ሀብት ከዜጎች በአደራ የተቀበልነው እንደመሆኑ የመንግስት ጥሬ ገንዘብና ቁሳዊ ንብረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤ ለዚህም የውስጥ ኦዲትን ለማጠናከር የባለሙያዉን አቅም የማጎልበት፣ በውጤት ላይ ያተኮረ የክዋኔ ኦዲትን በስፋት የማከናወን፣ የኦዲት መዋቅሩን፣ የግዥ ኦዲት ስራን፣ የክትትል ኦዲት ተግባርን የማጠናከር ስራዎችን መተግበር፤

- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥርን ለማጠናከር የአስፈጻሚ አካላትን የሰው ኃይል አቅም የማዳበር ስራዎችን በስፋት ማከናወን፣
- የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እና የማህበራዊ ተሳትፎ ስራዎች እንዲጎለብቱ ማድረግ፣ እና
- የተጠያቂነት ስርዓቱን በማጠናከር የተሰጣቸውን ኃላፊነት/አደራ በአግባቡ ያልተወጡ የአስፈጻሚ አካላት እንዲጠየቁ የማድረግ ስራን አጠናክሮ መቀጠል፣ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

# የ2010 ማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ዕይታ

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የቅርብ ዓመታትን የአገራችንን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና በፋይናንስ ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን ከዚህ በላይ ለማመልከት ሞክሪያለሁ፡፡ በቀጣይ የቀጣዩ ዓመት የፌዴራል መንግሥት በጀት የተመሰረተበትን ነባራዊ ሁኔታ በተሟላ ለመገንዘብ እንዲረዳ የያዝነውን በጀት ዓመት የእስካሁን የኢኮኖሚና የፋይናንስ አፈጻጸም ግምገማን በአጭሩ አቀርባለሁ፡፡

በመገባደድ ላይ ባለው የ2010 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ፈጣን ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የተተነበየ ሲሆን፣ ይህም በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ሁለንተናዊ ጠንካራ አፈጻጸም እንደሚደገፍ ይጠበቃል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተያዙ ዕቅዶች ስኬት በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚያሳዩ መረጃዎች በአመዛኙ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚገኙ ቢሆንም ከወዲሁ በሚታወቁ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ለምክር ቤቱ ዕይታውን ማመላከት ተገቢ ነው፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የመኸር ምርት ዳሰሳ ሪፖርት በዘንድሮው ዓመት ከዋና ዋና የመኸር የሰብል ምርት 306.1 ሚሊዮን ኩንታል እንደሚሰበሰብ በዳሰሳ ጥናቱ ይፋ ያደረገ ሲሆን፣ ይህ ምርት ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ምርት ጋር ሲነጻጸር የ5.4 በመቶ ብልጫ እንዳለው አመላክቷል፡፡ በአንጻሩ በዓመቱ ተከስቶ የነበረው አለመረጋጋት በኢንዱስትሪ እና በአገልግሎት ዘርፎች ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረ ይገመታል፡፡ በመገባደድ ላይ ባለው የበጀት ዓመትም አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ያልቻለው የውጭ ንግድ፤ ይህንንም ተከትሎ የተከሰተው የውጭ ምንዛሬ እጥረት በምርትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የፈጠረው መስተጓጎል በኢኮኖሚ ዕድገቱ ላይ የራሱን አሉታዊ ጫና ሊያሳድር እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ እንደዛም ሆኖ ኢኮኖሚው በ2010 በጀት ዓመት ፈጣን ዕድገት ማስመዝገቡን እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡

ባለፉት ዓመታት በኤክስፖርት አፈጻጸም ረገድ የታየው መቀዛቀዝ በ2010 በጀት ዓመትም መሰረታዊ መሻሻል አላሳየም፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ዘጠኝ ወራት ከወጪ ንግድ 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፡፡ ይህም በ2009 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተገኘው 1.95 ቢሊዮን ዶላር የወጪ ንግድ ገቢ ጋር ሲነፃጸር በ4 በመቶ ያህል ብቻ ከፍ ያለ ነው፡፡ በኤክስፖርት ዘርፍ የታየው ደካማ አፈጻጸም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ዘላቂነት ከፍተኛ አደጋ ውስጥ የከተተው መሆኑ በውል ግንዛቤ ሊወሰድበት እና ከአሳሳቢነቱ ጋር የሚመጣጠን ርብርብ ሊደረግበት ይገባል፡፡

በመንግሥት በጀት አፈጻጸም ረገድ፣ በ2010 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት ከታክስ፣ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እና ከውጭ ቀጥታ በጀት ድጋፍ ብር 140 ቢሊዮን የፌዴራል መንግስት ገቢ ተሰብስቧል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ከነዚህ ምንጮች ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው የዓመቱ በጀት (ተጨማሪ በጀትን ጨምሮ) ጋር ሲነጻጸር የ58.8 በመቶ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡ ከዚህ በላይ ለማብራራት እንደተሞከረው በያዝነው በጀት ዓመት የታክስ ገቢ አፈጻጸሙ ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ እጅግ ደካማ እንደነበረ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ከታክስ ገቢ ከብር 50 ቢሊዮን በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር እንደሚችል ተገምቷል፡፡ ይህም በመንግስትም ሆነ በታክስ መዋቅሩ ታክስ ለመሰብሰብ የነበረው ቁርጠኝነት ደካማ በመሆኑ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡

ከወጪ በጀት አንጻር በ2010 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት ለፌዴራል መንግሥት መደበኛ፣ ካፒታልና ለክልሎች ጠቅላላ የበጀት ድጋፍን ጨምሮ በድምሩ ብር 211 ቢሊዮን ወጪ ተደርጓል፡፡ ይህም በበጀት ዓመቱ ተጨማሪ በጀትን ጨምሮ ከታቀደው ብር 313.4 ቢሊዮን ጠቅላላ ወጪ (የፕሮጀክቶች ዕርዳታን ሳይጨምር) ጋር ሲነጻጸር 67.3 በመቶ አፈጻጸም ያሳየ ሲሆን፣ በ2009 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው የወጪ አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በ21.4 በመቶ (በ37.1 ቢሊዮን ብር) ብልጫ አለው:: ከዚህ ወጪ ውስጥ ከትሬዠሪ ለክልሎች ድጋፍ ብር 88.6 ቢሊዮን የተላለፈ ሲሆን፣ ይህም ከተያዘው የዓመቱ በጀት 77 በመቶው ሲሆን፣ የአጠቃላይ ወጪውን 42 በመቶ ድርሻ ይዟል፡፡ በወጪ ረገድ በታክስ ገቢ አሰባሰቡ ከታያው እጅግ ዝቅተኛ አፈጻጸም አንጻር ከፍ ያለ መጠን ያላቸው ወጪዎችን ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት ማስተላለፍ የግድ እንደሆነ ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

በአጠቃላይ እየተገባደደ ባለው የ2010 በጀት ዓመት ከማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች አንጻር በታክስ ገቢ፣ በኤክስፖርት እና በውጭ ዕዳ ጫና የታዩ አሳሳቢ አፈጻጸሞች የመንግስትን ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ መሆናቸውን ማስገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡ የታክስ አሰባሰብ ዝቅተኛ አፈጻጸም በማሳየቱ በመንግስት ወጪ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በኤክስፖርት ረገድ የታየው አፈጻጸምም መሰረታዊ ለውጥ የታየበት

ባለመሆኑ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት የተገኘው መጠን ላይ ለመድረስ እንኳን ብዙ የሚቀር መሆኑን መረጃው ያስረዳል፡፡ የኤክስፖርት መቀዛቀዙም በገቢ ዕቃዎች ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ከውጭ መግባት ያለባቸውን መሰረታዊና የልማት ዕቃዎች ማስገባት ከአለመቻሉም በላይ ከገቢ ዕቃዎች የሚሰበሰበውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አፈጻጸም ሊጎዳ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት ሁለት ወራት የታየው የዋጋ ዕድገት የዋጋ ግሽበት እንዳያስከትል አስፈላጊውን የፖሊሲ እርምጃ ተግባራዊ በማድረግ ለመቆጣጠር ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

## የ2011 የፌዴራል መንግስት በጀት

### የተከበሩ አፈ ጉባኤ

### የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከዚህ ቀጥሎ የማቀርበው የ2011 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀትን ለማዘጋጀት የተወሰዱ ዋና ዋና ታሳቢዎችንና ዝርዝር መግለጫዎችን ይሆናል፡፡ የ2011 በጀት ዓመት የሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አራተኛ ዓመት ነው፡፡ ይህ የ2011 የፌዴራል መንግስት በጀት ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በጀቱን ለማዘጋጀት የሚከተሉት የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ታሳቢ ተደርገዋል፣

- ባለፉት ዓመታት የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይ እንደሚሆንና በ2011 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በተመለከተው ግብ አንጻር በ11 በመቶ እንደሚያድግ ታሳቢ ተደርጓል፤
- የዋጋ ዕድገትም በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠው ግብ መሠረት በ2011 የ8 በመቶ አማካይ የዋጋ ዕድገት እንደሚኖር ታሳቢ ተደርጓል:: በያዝነው የ2010 በጀት ዓመት እስካሁን የታየው የዋጋ ዕድገት ለ2011 ከተያዘው ግብ አንጻር በተወሰነ መልኩ ከፍ ያለ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ እየተረጋጋ እንደሚሄድ ተገምቷል፡፡
- ከዚህም ጋር ተያይዞ የአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት በጊዜው የገበያ ዋጋ (nominal GDP) በ2011 በጀት ዓመት የ19 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ግምት ተወስዷል፡፡
- በ2011 በጀት ዓመት የገቢ ዕቃዎች ወጪ (Value of goods import) የ9.7 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው እና ይህም ከገቢ ዕቃዎች ለሚሰበሰበው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መሰረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የ2011 የውጭ ምንዛሬ ትንበያ ለበጀቱ ታሳቢ ተወስዷል፡፡

ከላይ የተገለጹት የ2011 በጀት የተመሰረተባቸው አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ሲሆኑ፣ በፊስካል ፖሊሲው ረገድ በጀቱ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ማዕከል ያደረገ እንዲሆንና የፈጣንና ዘላቂ ልማቱን፣ የድህነት ቅነሳን፣ እንዲሁም ትራንስፎርሜሽንን የሚደግፍ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በ2010 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 201 ቢሊዮን የፌዴራል መንግሥት የታክስ ገቢ በጀት ውስጥ ከብር 50 ቢሊዮን በላይ እንደማይሰበሰብ እና ለ2011 የተያዘው የታክስ ገቢ ግምት ከ2010 አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በጣም የተለጠጠ ዕቅድ እንደመሆኑ መጠን የታክስ አስተዳደሩን በልዩ ሁኔታ ማጠናከር የሚጠይቅ ነው፡፡ እንዲሁም እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የታክስ ገቢ አቅም እንደሚፈጥርና አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ግምት ውስጥ ገብቷል፡፡ ለታክስ ገቢ አሰባሰቡ መጠናከር የታክስ አስተዳደሩን አቅም በመሠረታዊነት ለመቀየር የሚያስችል የአቅም ግንባታና ሌሎች ድጋፎች የሚደረግ ሲሆን፣ መንግስት የታክስ አጀንዳን ቅድሚያ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡ መላ የኢትዮጵያ ህዝቦችና ግብር ከፋዮችም ለበጀት ዓመቱ የተያዘው የታክስ ገቢ ተሟልቶ እንዲሰበሰብ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከላይ የተዘረዘሩትን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የፌዴራል መንግስት የ2011 በጀት ዓመት ገቢ የውጭ ዕርዳታን ጨምሮ ብር 254.8 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል፡፡ ይህም በያዝነው በጀት ዓመት የታወጀውን ተጨማሪ በጀት ጨምሮ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ገቢ ጋር ሲነጻጸር የ1 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው የተገመተ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ ከተገመተው አንጻር ደግሞ የ11.9 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ተገምቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ የታክስ ገቢው ብር 211.1 ቢሊዮን እንደሚሆን የታቀደ ሲሆን፣ ለ2010 በጀት ዓመት ከተያዘው በጀት አንጻር የ5.2 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ ሆኖም በ2010 ይሰበሰባል ተብሎ ከሚጠበቀው አንጻር በ2011 የተያዘው የታክስ ገቢ ዕቅድ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፡፡ በመሆኑም ይህንን በመገንዘብ ዕቅዱን ለማሳካት ከአሁኑ የተለየ የአመራር ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን ማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች በአመዛኙ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሚገኘው የዘቀጠ ትርፍ፣ ከመንግስት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ በ2011 በጀት ዓመት ጠቅላላ ብር 24.6 ቢሊዮን ያህል ገቢ እንደሚገኝ ታቅዷል፡፡ በ2010 በጀት

ዓመት የታወጀውን የተጨማሪ በጀት ጨምሮ ከዚህ የገቢ ምንጭ ብር 34.5 ቢሊዮን እንደሚሰበሰብ የታቀደ ሲሆን፣ በ2011 በጀት ዓመት ይህ መጠን በ28.6 በመቶ የሚቀንስ ይሆናል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በ2010 በጀት ዓመት ለተጨማሪ በጀት ወጪ መሸፈኛ ከመንግሥት ድርጅቶች ሽያጭ (ፕራይቬታይዜሽን) ገቢ ዕቅድ በመያዙና በ2011 ከዚህ የሚጠበቅ ገቢ ባለመኖሩ እንዲሁም ሊገኝ የሚችለው የዘቀጠ ትርፍ ገቢ ሊቀንስ እንደሚችል በመገመቱ ነው፡፡

ከውጭ ሊገኝ የሚችለው ሀብት ከልማት አጋሮች በሚገኝ መረጃና የፋይናንሱን የፍሰት ታሪክ በማየት የሚሰላ ነው፡፡ የዚህ ገቢ ምንጭ በሁለት መልክ የሚፈስ ነው፡፡ እነዚህም የቀጥታ በጀት ድጋፍ (የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ድጋፍ) እና የፕሮጀክቶች ዕርዳታ ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው የዕርዳታ ምንጭ የሚገኘው ገቢ በቀጥታ ወደ ፌዴራል መንግሥት ግምጃ ቤት የሚፈስና መንግሥት የበጀት ድልድል የሚያደርግበት ሲሆን፣ ከዚህ ምንጭ በዕርዳታ መልክ ለ2011 በጀት ዓመት ይገኛል ተብሎ የታቀደው ገቢ ብር 2.3 ቢሊዮን ነው፡፡ እንዲሁም ከፕሮጀክቶች ጋር ቁርኝት ያለው ዕርዳታ በበጀት ዓመቱ ብር 16.8 ቢሊዮን እንደሚሆን ታቅዷል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የፌዴራል መንግሥት የ2011 በጀት ዓመት የወጪ በጀት ድልድል የምንከተለውን የፊስካል ፖሊሲ መሰረት ያደረገ ሲሆን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ቁልፍ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫና ዓላማዎችን እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፉን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህ መሰረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ከማሳካት አንፃር፣ ከመንግሥት የፋይናንስ አቅም፣ መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ተልዕኮና ኃላፊነት አኳያ ለውጤቶች፣ ለዋና ዋና ተግባራትና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ በመገምገም በጀቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ መ/ቤቶች ለፕሮግራም በጀት ዝግጅት እንዲረዳ አመልካች የበጀት ጣሪያ ከዝርዝር መመሪያ ጋር እንዲደርሳቸው ከተደረገ በኋላ በበጀት ጥሪው መሰረት አስፈፃሚ መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄያቸውን አቅርበው በዚሁ ላይ በመመስረት የበጀት ስሚ ተከናውኗል፡፡

የወጪ በጀቱ የተዘጋጀው የፕሮግራም በጀት አሰራርን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በጀቱ ግብዓትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ፣ ውጤትን በመለካት፣ ተጠያቂነትን በማስፈን፣ ፖሊሲና

ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና የመደበኛና የካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

የ2011 የወጪ በጀት ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፤ ዘላቂ የልማት ግቦችንና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ዓላማና ግቦችን ለመተግበር በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የበጀት ጥያቄያቸውን በተሰማሩበት መስክ ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ተግባራትን እና ፕሮጀክቶችን አካተውና ቅደም ተከተል ሰጥተው እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የተዘጋጀው የ2011 የፕሮግራም በጀት የሚከተሉትን በዋናነት ታሳቢ አድርጓል፡፡

- የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን(GTP II)፣ ግቦችን እንዲሁም የተደረሰበትን አፈጻጸም ታሳቢ በማድረግ፣
- ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ እየተተገበረ የሚገኘው የወጪ ቅነሳ ስልት በቀጣይ ዓመትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፤ ይህም የአስፈጻሚ መ/ቤቶች ውስን የሆነውን ሀብት ለታለመለት ዓላማ ብቻ በቁጠባ የመጠቀም ባህልና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ወጪ መቀነስ እንደሚችሉ ታሳቢ በማድረግ፣
- የ2011 በጀት ዓመት የሶስተኛው ዙር የፕሮግራም በጀት የሁለተኛ ዓመት እንደመሆኑ ለ2010-2012 የፕሮግራም በጀት ዘመን መ/ቤቶች ካስቀመጡት ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ግቦችና ከሚጠበቁ ውጤቶች አኳያ እና የ2010 የስድስት ወራት አፈጻጸምን በመገምገም የ2011 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል፡፡

እነዚህ ከላይ የዘረዘርኳቸው የአጠቃላይ የወጪ በጀት ዝርዝር ታሳቢዎች ሲሆኑ የመደበኛ በጀቱ የተመሰረተባቸው ዋና ዋና ታሳቢዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በቀጣይ መንግስት ተቋማዊ ተልዕኮን በላቀ ደረጃ መፈጸምና ከፍተኛ የወጪ ቁጠባና ወጤታማነት ማረጋገጥ ላይ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ ታሳቢ በማድረግ፣ እንዲሁም ባለበጀት መ/ቤቶች የመንግስት ፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓትን በተጠናከረ መልኩ እንደሚተገብሩ ታሳቢ በማድረግ፣
- የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት፣
- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች የመከላከልና አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት ስራ በመንግስት በኩል በቀጣይ ለሚሰሩ ስራዎች የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ፣

እንዲሁም የካፒታል በጀት ድልድሉም ቀጥሎ የተመለከቱትን ዋና ዋና ታሳቢዎች መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

- የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘላቂ ልማት ዘርፎች እና ማህበራዊና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የግብርና ምርታማነትን፣ የመስኖ ልማት እና የስራ ዕድል ፈጠራ ግቦችን ለማሳካት እንዲያስችሉ በዕቅዱ የመጀመሪያ ሶስት ዓመታት ለተጀመሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ እንዲሁም በዕቅዱ ዘመን እንዲገነቡ ታቅደው እየተገነቡ ላሉ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች አስፈላጊውን በጀት በመደገፍ፣
- በውጭ ፋይናንስ ጭምር ለሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የውጭ ፋይናንስ ፍሰት በእርግጠኝነት በበጀት ዓመቱ ሊፈስ የሚችለውን የገንዘብ መጠን በበጀት እንዲያዝ በማድረግ፣ እና በውጭ ፋይናንስ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ከመንግስት የሚያስፈልገውን ተጓዳኝ ፋይናንስ እንዲያዝ በማድረግ፣
- ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ በነባር ዩኒቨርሲቲዎች ለትምህርት ጥራት አጋዥ ለሆኑ ወርክሾፕ፣ ላብራቶሪ እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ለማደረጀት እና ያሉትን ነባር ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ እንዲሁም ለአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ከተማሪ ቅበላ አኳያ ለግንባታ እና ፋሲሊቲዎችን ለማደራጀት የሚያስፈልገውን በጀት ታሳቢ በማድረግ፣
- መንገድን በተመለከተ ነባር ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ እና በውጭ ፋይናንስ ለሚካሄዱ አዳዲስ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ፣
- የውሃ መስኖ ልማት እና የግብርና ዘርፍ ልማትን ከማፋጠን አንጻር በበጀት ድልድሉ ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ የካፒታል በጀቱ ተዘጋጅቷል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ዋና ዋና ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የቀረበው አጠቃላይ የፌዴራል መንግሥት የ2011 በጀት ብር 346.9 ቢሊዮን ሲሆን ይህም ከ2010 ወጪ በጀት ጋር ሲነጻጸር በብር 12.1 ቢሊዮን ወይም የ3.6 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ ከዚሁ በጀት ለመደበኛ ወጪ ብር 91.7 ቢሊዮን፣ ለካፒታል ብር 113.6 ቢሊዮን እንዲሁም ለክልል መንግሥታት ድጋፍ ብር 135.7 ቢሊዮን እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ብር 6 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል፡፡

ተደግፎ ከቀረበው ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ለክልል መንግሥታት የተመደበው የበጀት ድጋፍ ሲሆን፣ ይህም የጠቅላላ በጀቱ 39.1 በመቶ ነው፡፡ ይህም የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት

ድጋፍ ለ2010 ከተያዘው ጋር ሲነጻጸር 15.7 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ ለ2011 በጀት ዓመት ለፌዴራል መንግስት የካፒታል በጀት የተደለደለው በሁለተኛ ደረጃ ሲገኝ ድርሻው 32.7 በመቶ ሆኗል፡፡ ለ2011 በጀት የተደለደለው የካፒታል ወጪ በጀት ለ2010 ከተያዘው ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡ የካፒታል በጀት ወጪ አሸፋፈኑም ከአገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢና ከውጭ አገር በሚገኝ ዕርዳታና ብድር ሲሆን ከመንግስት ትሬዠሪ፣ ከእርዳታ እና ከብድር እንደሚሸፈን የተያዘው የካፒታል ወጪ በጀት በቅደም ተከተል ብር 76 ቢሊዮን (66.9 በመቶ)፣ ብር 16.3 ቢሊዮን (16.4 በመቶ) እና ብር 21 ቢሊዮን (18.5 በመቶ) ነው፡፡ በሌላ በኩል ለመደበኛ ወጪ የተደለደለው በጀት ከአጠቃላይ ወጪ በጀት ድርሻው 26.4 በመቶ ሲሆን ለ2010 ከተመደበው የተስተካከለ በጀት አንጻር የ4.4 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል፡፡

ከአጠቃላይ የ2011 መደበኛና ካፒታል በጀት ውስጥ 66 በመቶ ድርሻ ያላቸው ትምህርት፣ መንገድ፣ ግብርና፣ ውሃ፣ ጤና፣ ኢንዱስትሪ፣ ከተማ ልማት፣ የከተማ ምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጀቱ በዘላቂ ልማት፣ በኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እና በድህነት ተኮር ክፍላተ ኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት ላይ ያመዘነ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህም በላይ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ለሚያካሂዷቸው አጠቃላይ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልገውን የወጪ ፍላጎት ለመሸፈን እንዲቻል ከፍተኛ የበጀት ድጋፍ መመደቡን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በጥቅሉ የ2011 በጀት በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን አቅጣጫ ለመተግበር የሚያግዝ እንደሆነ ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደሞከርኩት በ2011 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ከሃገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እንዲሁም ከውጭ አገር ዕርዳታና ብድር በድምሩ ብር 287.6 ቢሊዮን ገቢ እንደሚሰበሰብ በዕቅድ ተይዟል፡፡ እንዲሁም ለመደበኛ፣ ለካፒታል እና ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍና የዘላቂ ልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪ ጠቅላላ ብር 346.9 ቢሊዮን በጀት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሠረት በታቀደው የፌዴራል ገቢና ተደግፎ በቀረበው የወጪ በጀት መካከል የብር 59.3 ቢሊዮን የበጀት ጉድለት ይታያል፡፡ ይህንንም የበጀት ጉድለት ከሃገር ውስጥ በሚገኝ ብድር ለመሸፈን ታቅዷል፡፡ የሀገር ውስጥ ብድር መጠኑ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር

2.3 በመቶ ሲሆን፣ ይህም የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ተግባራዊ ከሚደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ ከመሆኑም በላይ በዋጋ ንረት ላይ የጎላ ተፅዕኖ እንደማያሳድር ግምት ውስጥ ገብቷል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ለ2011 በጀት ዓመት የልማት ተግባራት ማስፈጸሚያ እንዲውል ተደግፎ የቀረበው የፌዴራል መንግስት በጀት ዝርዝር ከዚህ በላይ እንዳቀረብኩት ሲሆን፣ በጀቱ ለአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የሚያስፈልገውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ለተግባራዊነቱ ከመቼውም ግዜ በላይ መረባረብ እንደሚያስፈልግ ለተከበረው ም/ቤት እና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በሙሉ ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም በቀሪዎቹ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት እስከአሁን የተገኘውን መልካም ውጤት በማስቀጠልና ድክመት በታየባቸው የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ያላሳካናቸውን ግቦች ለማካካስ ከምንጊዜውም በበለጠ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ በማጠናከርና ተነሳሽነትን በማጎልበት የበለጠ ስኬት ማስመዝገብ ይኖርብናል፡፡

የመንግሥት ወጪ በጀት መጽደቅ የበጀት ኡደቱ መነሻ እንጂ በራሱ መጨረሻ እንዳልሆነ የሚታወቅ ሲሆን፣ በጀቱ ተግባራዊ የሚደረገው ዓመቱን በሙሉ በሚተገበረው የበጀት አስተዳደር ነው፡፡ በሚገባ ተሰልቶ፣ የመንግሥትን የልማት ፖሊሲ ግብና ዓላማ አገናዝቦ፣ በትክክለኛ አቅጣጫ የተቀመረው የመንግስት በጀት ተግባራዊነት የበጀት አስተዳደሩ የተሳለጠ ካልሆነ የሚፈለገውን ውጤት አያስገኝም፡፡ ይህን መሰሉ ኃላፊነት የሚወድቀው የበጀት ጥያቄያቸውን በትኩረት አቅርበው በውይይትና በመግባባት የተደለደለላቸውን በጀት የማስተዳደር ተግባር በሚያከናውኑ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት (የራሴን የሚኒስቴር መ/ቤት ጨምሮ) ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ ነው፡፡

የልማት ዕቅድን ለማስፈጸም እንቅፋት የሆኑብንን የማስፈጸም አቅም መዳከም፣ የፋይናንስ ውስንነት በተለይም የታክስ ገቢ ማነስ፣ ዝቅተኛ የአገር ውስጥ ቁጠባ፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ እና የወጪ ንግድ መዳከም ማነቆዎች ለመፍታት የተጠናከረ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ስለዚህም በጀቱን ካለፉት ዓመታት በተለየ መንፈስ ተፈጻሚ ለማድረግ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ::

ለ2011 ተደግፎ የቀረበው ይህ ረቂቅ የመንግስት በጀት ካለፉት ዓመታት በጀት ጋር ሲነጻጸር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን የያዝናቸውን የዘላቂ ልማትና ትራንስፎርሜሽን ግቦችና

ተጓዳኝ ተግባራትን ለማሳካት ከፍተኛ ሚናም ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በቁጠባና በላቀ ውጤታማነት ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ በተጨማሪም ባለበጀት መ/ቤቶች የሚመደብላቸውን በጀት የመንግስት ፋይናንስ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ህጎችን ብቻ ተከትለው ስራ ላይ እንዲያውሉ እያሳሰብኩ ይህንን ለማረጋገጥ እንዲቻል የሚደረገው የክትትልና የቁጥጥር ስራ እንደዚሁም የተጀመረው ተጠያቂነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ ለዚህም የተከበረው ምክር ቤት በቋሚ ኮሚቴዎቹ አማካኝነት የሚያደርገው ክትትልና ግምገማ አጋዥ ሆኖ እንደሚቀጥል ጽኑ እምነቴ ነው፡፡

በአጠቃላይ የ2011 በጀት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን እየተመኘሁ፣ የበጀት ዝግጅቱ የተሳካ እንዲሆን የበጀት ጥያቄያቸውን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና በተዘጋጀው የበጀት ሥርዓት መሰረት ላቀረቡ አስፈጻሚ አካላት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ በጀቱ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ በወቅቱ ለዚህ ምክር ቤት እንዲቀርብ በማድረጉ፣ ገቢ ሰብሳቢ ክፍሎችም ዝርዝር የገቢ ዕቅድ በማዘጋጀት እንዲሁም፣ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የበጀት መረጃዎችን ለሕዝብ በማስተላለፍ ላደረጉት አስተዋጽኦ በመ/ቤቴና በምክር ቤቱ ስም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህን ተደግፎ የቀረበውን የ2011 ፕሮግራም በጀት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያፀድቀው በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

**የላቀ ብሔራዊ መግባባትና ዲሞክራሲያዊ አንድነት**

**ለላቀ ሀገራዊ ስኬት!!!**

**በጀት ለውጤት!!!**

**አመሰግናለሁ፡፡**